# የኮሎራዶ የአሽከርካሪ የእግድ እና የክልከላ ፖሊሲ

የእኛን የመኪና ሹፌሮች እና የተሳፋሪዎችን ደህንነት ለመጠበቅ፣ Lyft የእግድ እና የክልከላ ፖሊሲ አዘጋጅቷል። ይህ ፖሊሲ እና የLyft የአገልግሎት ውሎች ለሁሉም አሽከርካሪዎች ተግባራዊ ይሆናሉ።

## እግድ እና ክልከላ ለምን ይከሰታል?

በ Lyft የአገልግሎት ውሎች መሰረት የተለያዩ መንስዔዎች ክልከላ (ከ72 ሰዓታት ላነሰ ጊዜ) ወይም የመለያ እግድ (በኮሎራዶ ግዛት ሕግ በተገለጸው መሰረት) ሊያስከትሉ ይችላሉ። ምሳሌዎችም የሚከተሉትን ያካትታሉ፣ ነገር ግን በእነዚህ ብቻ አይገደቡም፦

**የደህንነት ጉዳዮች**

ደህንነቱ ያልተጠበቀ አነዳድ፣ ትንኮሳ፣ ጥቃት እና መድሎ ስለመፈጸሙ በሚቀርቡ ውንጀላዎች ምክንያት ለደህንነት አስጊ የሆኑ አካላትን መፍትሔ ለመስጠት።

**በሕግ የሚጠየቁ መስፈርቶች**

አስፈላጊውን የዳራ/DMV ማጣሪያ መስፈርቶችን የማያሟሉ፣ ወይም ትክክለኛ ያልሆነ የአሽከርካሪ / ተሽከርካሪ ሰነድ ያላቸው አሽከርካሪዎች።

**ማጭበርበር**

ለምሳሌ ማንነቶችን በማጭበርበር ወይም በክፍያ ማጭበርበር እና/ወይም በሐሰተኛ ተግባር ላይ በመሳተፍ ለማጭበርበር የሚሞክሩ አሽከርካሪዎች።

**የመተግበሪያ ተሞክሮ**

መተግበሪያውን የሚጠቀሙ ተሳፋሪዎች በሚሰጡት ከባህርይ ጋር የተያያዘ ጥቆማ ምክንያት ከLyft ተደጋጋሚ ማስጠንቀቂያ የተሰጣቸው አሽከርካሪዎች።

---

የLyft የአገልግሎት ውሎች ጥሰትን መሰረት በማድረግ ለሚከናወኑ የመለያ እግዶች፣ የLyft መለያዎ ያለምንም የቅድሚያ ማስጠንቀቂያ ሊታገድ ይችላል። አሽከርካሪዎች በ 24 ሰዓታት ውስጥ በኢሜይል ወይም በመተግበሪያው አማካኝነት ስለ ክልከላው ወይም እገዳው መረጃ ይሰጣቸዋል።

የደህንነት ጉዳዮችን የተመለከቱ አብዛኛዎቹ ውንጀላዎችን በተመለከተ፣ Lyft በአሽከርካሪው መለያ ላይ ምርመራው እስኪጠናቀቅ ለሚወስደው ጊዜ ያክል ጊዜያዊ ክልከላ ይጥላል እንዲሁም ሁሉም ተሳታፊ ወገኖችን ለማነጋገር ይሞክራል። በአማካይ፣ የLyft ምርመራዎች ከ36 ሰዓታት ባነሰ ጊዜ ውስጥ ይጠናቀቃሉ፣ ነገር ግን በምርመራው መሰረት ረዘም ያለ ጊዜ ሊወስዱ ይችላሉ። የምርመራው ውጤቶች አሽከርካሪው በLyft መድረክ ላይ ማሽከርከር እንዲቀጥል የሚፈቅዱ ከሆነ ጊዜያዊ ክልከላው ይነሳል።

መደረግ የሚቻል ከሆነ፣ የመለያ እገዳው ውሳኔ ምርመራው በሚጠናቀቅበት ጊዜ ለአሽከርካሪው ይነገራል። አሽከርካሪዎች አዲስ ማስረጃ መቼ መቅረብ እንደሚችል መጠየቅን ጨምሮ እገዳውን ይግባኝ የማለት አማራጭ አላቸው። በይግባኝ ሒደቱ ላይ ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት፣ እባክዎ ከታች "የእኛ የይግባኝ ሒደት" የሚለውን ይመልከቱ።

ከደህንነት ወይም ማጭበርበር ጋር ላልተገናኙ ተደጋጋሚ የባህሪ ጥፋት ውንጀላዎች፣ ይህን ባህሪ እና ርዝመቱ የሚጨምር የአጭር ጊዜ ክልከላን፣ ከ12 ሰዓት ጀምሮ እስከ መታገድ የሚደርስ፣ በተመለከተ አሽከርካሪዎች በLyft መተግበሪያ ማሳወቂያዎች ሊደርሳቸው ይችላል።

## የእኛ የእግድ እና የክልከላ ሒደት

**የአሽከርካሪ መለያ (አካውንት) ማስጠንቀቂያ ሲኖርበት**

ተጠቃሚዎች ሪፖርት አድርገው ወይም በመተግበሪያው አማካይነት

**1**

**ጊዜያዊ ክልከላ**

ምርመራ በሚካሄድበት ወቅት ወይም አሽከርካሪው ጉዳዩን እስከሚያስተካክል ድረስ መለያውን ለጊዜው እንዳይሰራ ልንከለክል እንችላለን። አሽከርካሪው በኢሜይል፣ በስልክ ወይም በLyft መተግበሪያ በኩል እንዲያውቀው ይደረጋል።

**2**

**ማሻሻያ**

በአንዳንድ ሁኔታዎች (ለምሳሌ፣ ጊዜ ያለፈባቸው ሰነዶች ሲኖሩ)፣ አሽከርካሪዎች በመተግበሪያው አማካይነት የማሻሻያ ሒደቶችን ማጠናቀቅ ይችላሉ።

**በወኪል የሚካሄድ ምርመራ**

አንድ ክስተት ሪፖርት ሲደረግ ከሁለቱም የሚመለከታቸው ተጠቃሚዎች ዝርዝር መረጃ ለመሰብሰብ ቁርጠኞች ነን። ተጠቃሚዎች የዳሽ ካሜራ ቀረጻን፣ ፎቶዎችን፣ የፖሊስ ሪፖርቶችን እና ሌሎች ማረጋገጫዎችን እንዲያቀርቡ ይበረታታሉ። አጠራጣሪ/አጭበርባሪ የተሳሳተ ሪፖርቶችን በንቃት እንገመግማለን። አሽከርካሪዎች የምርመራ ስራውን ከሚያካሂደው ወኪል ጋር የስልክ ጥሪ ለማድረግ መጠየቅ ይችላሉ።

**3**

**ውሳኔ ማሳለፍና ማሳወቅ**

አሽከርካሪው ማሽከርከር መቀጠል እንደሚችሉ ወይም መለያው ስለመታገዱ የመጨረሻ ውጤቱን እናሳውቃለን።

---

## የእኛ የይግባኝ ሒደት

መለያ (አካውንት) ከአገልግሎት ውጭ ሲደረግ፣ የእኛ ግብ አሽከርካሪዎች ፍትሐዊ፣ ተጨባጭ እና ምክንያታዊ በሆነ የይግባኝ ሒደት ውስጥ ድጋፍ እንደሚደረግላቸውና ክብር እንደሚሰጣቸው እንዲሰማቸው ማድረግ ነው። ይህን ለማከናወን፣ አሽከርካሪዎች የእግድ ውሳኔዎችን ይግባኝ የሚሉበት በመተግበሪያ ውስጥ የተካተተ የማውጫ ቁልፍ ስራ አስጀምረናል። ይህ አዲስ ቻናል አሽከርካሪዎች ማንኛውንም አዲስ ወይም ወቅታዊ መረጃ ለLyft እንዲያቀርቡ፣ እንዲሁም መለያ (አካውንት) ከአገልግሎት ውጭ ሲደረግ ለሚቀርቡ ይግባኞች ድጋፍ የሚሰጥ ልዩ ቡድንን በቀጥታ ለማግኘት ያስችላቸዋል።

- አንድ አሽከርካሪ የእግድ ማስታወቂያ ሲደርሰው፣ ውሳኔው ድጋሚ እንዲታይለት መጠየቅ ይችላል።
- የLyft የደህንነት ቡድን የውሳኔ ግምገማውን በማካሄድ አዲስ ውሳኔ ላይ ለመድረስ እንዲያስችለው፣ አሽከርካሪዎች አዳዲስ ማስረጃ ወይም መረጃ እንዲያቀርቡ ይበረታታሉ።
- የመጀመሪያውን ውሳኔ የሚያስቀይር አዲስ ማስረጃ ወይም መረጃ ካለ መለያውን (አካውንቱን) ስራ ልናስጀምር እንችላለን።
- በውሳኔያችን ከጸናን፣ መለያው ታግዶ እንዲቆይ እናደርጋለን።
- በኮሎራዶ ሕግ መሰረት ተጨማሪ ጊዜ ካልተጠየቀ በስተቀር፣ ሁሉም የመጨረሻ ውሳኔዎች በ14 ቀናት ውስጥ ለአሽከርካሪው ይነገራሉ።

**በመተግበሪያው በኩል የሚቀርቡ ይግባኞች**

